### ግፈኝነት ይብቃ!

የዛሬ ዓመት፣ በሰሜን ዕዝ ላይ ከተደረገው ክህደት ጀምሮ፣ በሕዝባችን ላይ እየደረሰ ያለው ሰቆቃ፣ ክፋትና ጥፋት፣ በቅርብ ጊዜ ታሪካችን የመጀመርያው ነው። በየትኛውም ዘመን፣ ሕዝባችን በቋንቋ ወይም በጎሣ ማንነቱ ተለያይቶና ተፈራርጆ እንዲባላ የተደረገበት፣ የተፈናቀለበት፣ የተዘረፈበት፣ የተሰደደበት፣ የሞተበት፣ ክፉ ዘመን የለም። የቅርቡን ብናስታውስ እንኳን ኦሮሞዎች ከሱማሌ፣ ሱማሊዎች ከኦሮሞ፣ ወላይታዎች ከሲዳማ፣ጋሙዎች ከቡራዩ፣ አማራዎች ከኦሮሞ፣ ከደቡብ፣ ከቤኒሻንጉል፣ ከአጣዬ፣ ወዘተ ከብዙ ምሳሌዎች ጥቂቶቹ ናቸው። የችግራችን ሁሉ መሠረታዊ ምክንያት ግልፅ ነው፣ የጎሣ ፖለቲካ ነው።

የጎሣ ፖለቲካ ትግራይን ጨምሮ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ አጎሳቅሏል። የበለጠ የተጎዳው ግን አማርኛ ተናጋሪው ነው። መነሻ ምክንያቱ፣ በአድዋ ጦርነት አንድ አውሮፓዊ መንግሥት በአንድ ጥቁር ሀገር መሸነፍ ነው። አጥንተን ደረስንበት ያሉትን የሽንፈታቸው ምክንያት የሕዝባችንና መሪዎቻችን በአንድነት መቆም ነው። ምሳሌነቱ በወቅቱ በነጮ ቅኝ አገዛዝ ሥር ለወደቀው አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ስለነበር፣አንገቷን ቀና ያደረገቸው ኢትዮጵያ መደፈቅ ነበረባት። መፍትሔ ያሉት ሕዝቧን የመከፋፈል ዘዴ ማቅረብ ነበር። የቀረበው ምክረ ሃሳብ አማራውን ጨቋኝና ጭራቅ አርጎ መሳል ነበር። ይህንን ጣልያኖች በሁለተኛው ወረራቸው ወቅት በሰፊው ተጠቅመውበታል። የበቀል ትርክቱ ቀደም ቢኖርም, ተባብሶ የቀጠለው ከዚህ በኋላ ነበር።

ስሁት ትርክቱ በተለይ ላለፉት 50 ዓመታት ሕዝባችን ለፍትሐዊ አስተዳደር የሚያደርገውን ትግል ተከትሎ ሰርጎ ገባ። እርምት ሳይደረግበት እስከዛሬ ዘልቋል። የጎሰኝነት አክራሪነት መደበኛ ርዕዮት እስኪመስል ድረስ ድረስ ተገፍቷል። ጨካኙን የደርግ መንግሥት ለመጣል በተደረጉት ትግሎች፣ የ'ብሔር ኃይሎች' የተሻለ ጉልበት ስላገኙ መንግሥት መሠረቱ። ብሔርተኝነት ከተራ ትርክትነት ወደ ሕጋዊነት ተሸጋገረ። በመቶ ሸህ የሚቆጠሩ አዲስ ቢሮክራሲ፣ አዲስ የጥቅም መደብ ፈጠሩ ። ሥልጣንን ተጠቅሞ አዲሱ የጥቅም መደብ ሀብት ለመሰብሰብ፣ ለመክበር የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ይበልጥ አመች ሆነ። ዛሬ የሚደረገው ትንቅንቅ አንድም፣ ከአክራሪ ብሔርተኝነት የሚመነጨውን ጥቅም ለማስቀጠል ከሚታገል መደብ ጭምር ነው። ከዚህ ይልቅ፣ አንድነትና መተባበር ቢኖር ኑሮ፣ የሀገራችን ዕድገት አሁን ካለንበት እጅግ የተሻለ ይሆን ነበር።

የሚገርመው፣ በዓለም ዙርያ ያሉ ሀገሮች አብዛኛዎቹ አዳዲስ ናቸው። እንደኛው የብዙ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች ናቸው። ብዙዎቹ እንደኛው የሚያቆራኛቸው ታሪካዊ መሠረቶችም ሆኑ ተወራራሽ ዕሴቶች የሏቸውም። ግን፣ ሀገር መንግሥቶቻቸውን የመሠረቱት ፣ በዜግነት ማንነት እንጂ በየጎሣ ማንነታቸው አይደለም። አገር እየጠቀሱ፣ ስዊትዘርላንድ፣ ሕንድ ካናዳ፣ ስካትላንድ እንዲህ ነው፣ እንዲያ ነው ፣ ወዘተ እያሉ የሚያምታቱትን ዘር በሉ በሏቸው። የሚናገሩትን አያውቁም። የየሀገሮቹን ታሪክ አያውቁም። በየትኛዎቹም ሀገሮች ችግሮቻቸውን የፈቱት በዜግነት ሕጎች ጠለላ ሥር መሆኑን፣ ሕዝብን ለጎሳ ፖለቲካ መከፋፈል ወንጀል መሆኑን አይረዱም።


Website:
Ethiopiawin.net

800 375 4062
email: ethiopiawinnet@gmail.com

Ethiopiawinnet North America
P O Box 171
E. Lansing, MI 48823

ከተለያዩ ሀገሮች ሕጎች፣ አሰራሮችና ልምዶች እንማር ብንል እንክዋን ፣ እስካሁን ተማርን ያልነውን የተዛቡ የፖለቲካ እምነቶች መተው አለብን። ትምህርት ለሀገር የሚበጀው፣ ከሀገራችን ባህል፣ ዕሴቶችና ዘላቂ ጥቅሞች ጋር ሲዛመድ ብቻ ነው።

አንድ ዓመት ያደረገው ጦርነት ከሰኔ ወር ጀምሮ ከትግራይ ወደ አማራና አፋር ክልሎች ተስፋፍቷል። ዛሬ በሚልዮን የሚቆጠር ወገናችን ለረሃብ፣ መፈናቀል፣ ስደት፣ የንብረት ውድመት፣ተጋልጧል። የዓለም አቀፍና የሀገር ቤት ዘጋቢዎች፣ ዓይን እማኞችን በመጥቀስ እንዳቀረቡት፣ ተሰምቶ የማይታወቅ ዓይነት አረመኔነት እየታየ ነው። **ማይካድራ፣ ጋሊኮማ፣ አጋምሳ፣ ቆቦ፣ ዉጫሌ መርሳ፣ ጭና፣ ተሁለደሬ፣ ደሴ፣ ኮምቦልቻ፣ ሀርቡ ፣ ከሚሴ** - ወጣቶችን በመረሸን፣ እናቶችን፣ ልጃገረዶችን፣ በባሎቻቸው፣ ታዳጊዎች እናት አባቶቻቸው ተገደው እያዩ ፣ መነኩሲቶችንም ጭምር መድፈር፣ የሴቶችን የግል ጌጦጣቻቸውን ሳይቀር መዝረፍ፣ ወጣቶችን ነጥሎ ማሰር፣ መረሸን፣ ቀምቶ መብላት፣ የበሉበትን ማዕድ መሰባበር፣ የሞተባቸውን አርሶ አደሩ ቤት ውስጥ መቅበር፣ ብሔራቸውን በስም እየጠሩ መስደብ፣ ማንቋሸሽ፣ ማዋረድ፣ ቤት ማቃጠል፣ የደረሰን ሰብል አጭዶ መውሰድ፣ እንስሳትን መግደል፣ ቅርሶችን መዝረፍ፣ ማቃጠል፣ በጋሊኮማ እንደታየው፣ ሕፃናትንና አረጋውያን፣ሴቶች የተጠለሉበትን ሰላማዊ የስደተኛ ካምፖችን በከባድ መሳርያ ተኩስ ማውደም፣ በደሴ እንደታየው ፅኑ ህሙማንን አይሺ ነቅሎ መግደል፣ የሃይማኖት ተቋማትን ማራከስ፣ እረ ስንቱ !

እኒህ ዲያቢሎሲያዊ ተግባራት በአማራና አፋር ክልሎች ብቻ የተወሰኑ አልነበሩም። የሰብአዊ መብት ጥሰቶቹም በትሕነግ ብቻም የተከናወኑ አይደሉም ። ሌሎችም አሉበት። በተለያዩ መጠኖች፣ በተለያዩ ቡድኖች፣ በቤኒሻንጉል፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በደቡብ ተካሂደዋል ። ብዙዎችን የሚያመሳስላቸው፣ ብሔር ተኮር፣ በተለይም አማራ ተኮር መሆናቸው ነው። ብሔር ለይቶ፣ አሸማቃቂ ቅፅል ደርቶ፣ ዜጎችን ማጥቃትና በጠላትነት መፈረጅ በእግዚአብሔር ቤት ኃጥያት ነው። በምድራዊ ሕግም ወንጀል ነው። በቅጡ ከተያዘ ዜግነት እኮ በራሱ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ያካተተ፣ የመብቶች ሁሉ ራስ ነው። ግፍ ይብቃ!

መርሳት የሌለብን፣ በትህነግ የሚቀነባበረው ጦርነት በሞቶ ሸህ የሚቀጠሩ የትግራይ ወጣቶቻችንን በልቷል። እየበላም ነው። ጉዳቱ የሁላችንም ነው። የክልሉ ሕዝብ ትሕነግን የሚደግፈው በአብዛኛው ተገዶ ነው የሚል ግምት አለ። ሕወሓት ከሚታወቅባቸው ባህርያት አንዱ ሕዝብን ማስገደድ ነው። የምናየው ነው፣ የተራው የትግራይ ሕዝብ የኑሮው ሁኔታ እጅግ ጎስቋላ ነው። አንዳንድ ብዥታዎች ቢኖሩም፣ ለዘለቄታው፣ ለትግራይም ሆነ ለሌላው የሀገራችን ወጣት፣ ሰፋ ያሉ የዜግነት፣ የታሪክና የኢትዮጵያዊነት ትምህርቶች ሊዘረጉለት ይገባል። እንደተጀመረው ለለውጡ በቅንነት አብረን ከሰራን፣ ኢትዮጵያችን ሰፊ ናት፣ ለሁላችንም ትበቃለች።

በዚህ አጋጣሚ፣ ሰሞኑን፣ የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ካውንስልና የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ስለትግራይ በጋራ ያወጡትን የምርመራ ሪፖርት እንደግፋለን። በቀጣይ፣ በአፋር፣ አማራ፣ በቤኒሻንጉል፣ ኦሮምያ፣ ሱማሌ፣ ደቡብ፣ ወዘተ ወስጥ ቤተደረጉት የመብት ጥሰቶች ላይ ምርመራ እንዲደረግ እንጠይቃለን።

የጎሣ ፖለቲካ መጨረሻው ግድያ፣ ውድመት፣ አገር ማፍረስ ነው። ከኢትዮጵያ በስተቀር በዓለም ዙርያ በሕግ የተከለከለ ነው ። ስለሕውሃት የፖለቲካ ኃጢያት ብቻ ማውራት የኛ ምርጫ አልነበረም። ድርጅታችን ከፓርቲ ፖለቲካዎች ገለተኛ ነው። የሚካሄዱት ነገሮች ግን እጅግ ፀያፍ ወንጀሎች ናቸው።

በዓይነትም፣ በክፋት መጠንም ታይተውም፣ ተሰምተውም የማያውቁ፣ ዘግናኝ፣ ፀረ ኢትዮጵያ ናቸው። በየትም ሀገር የቅርብ ጊዜ የሰው ልጅ ታሪክ ያልተሰሙ ናቸው። አንድ መባል ስላለባቸው ነው። የማሕበረሰብ (ሲቪክ) ድርጅታችን በማንኛውም የፖለቲካ ፓርቴ በተለይም በትሕነግ የሚካሄዱትን አሰቃቂ ዘር ተኮር ሰብዓዊ መብት ጥሰቶችና ወንጀሎች አጥብቀን እናወግዛለን።

በዚህ አጋጣሚ፣ በዓለም ዙርያ ያሉ፣ በጎ አመለካከት ያላቸው ሀገሮችና የዓለምሕዝብ፣ ከታሪካዊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንዲቆሙ እንጠይቃለን። በዚህ የዘር ጥላቻ ጦርነት በሚሊዮን የምቆጠሩ አማራዎችና አፋሮች ከቀያቸው ተሰደው በከፍተኛ ችግር ስለሚገኙ፣ ሰብዓዊ  እርዳታዎች በያይነቱ እንዲደርሳቸው ፣ በውጭም በውስጥም ያሉ የረዲኤት ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ሕዝብ ርብርብ እንዲያደርጉ እናሳስባለን።

ኢትዮጵያዊነት ይለምልም!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!